መልእክት ሦስት

**በብሉይ ኪዳን ያለው የኢዮብ የእግዚአብሔርን**
**መጨረስ (consuming) እና መግፈፍ ልምምድ**
**በአዲስ ኪዳን ካለው ከጳውሎስ የራቀ መሆኑ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኢዮብ 3፡1፤
2 ቆሮ. 4፡10-12፣ 16-18፤ ፊልጵ. 1፡19-25፤ 4፡4

1. **ኢዮብ ምንም እንኳን ፍጽምናው፣ ቅንነቱ እና ግብረገባዊነቱ ቢኖሩም በንብረቱ እና በልጆቹ ላይ ባጋጠመው መዓት እና በአካሉ ላይ በወረደው መቅሰፍት በመንዳቱ ፈጽሞ ተረብሾ፣ ግራ ተጋብቶ እና ተወሳስቦ ነበር፦**

   ሀ. ኢዮብ እናቱን ከመርገም ጋር እኩል የሆነውን የተወለደበትን ቀን ሲረግም፣ በእርግጥም ፍጹም እና ቅን አልነበረም፣ ወይም ግብረገባዊነቱን አልጠበቀም፤ ይልቁንም ግብረገባዊነቱን ያጣ ሆነ—ኢዮብ 3፡1።

   ለ. የእግዚአብሔር ውጥን በፍጽምናው እና በቅንነቱ ፍጥረታዊውን ኢዮብ ማፈራረስ ነበር ይኸውም ኢዮብን በኢኮኖሚው መሠረት በእግዚአብሔር የተቀናበረ የእግዚአብሔር ሰው ለማድረግ በእግዚአብሔር ተፈጥሮ እና ባሕርያት የታደሰ ኢዮብን መገንባት ይችል ዘንድ ነው፤ እንዲህ ያለው ሰው (እንደ ጳውሎስ ያለ) መወለዱን እስኪረግም እና ከመኖር ይልቅ መሞትን እስኪመርጥ ድረስ በማንኛውም መከራ እና ችግሮች ፈጽሞ አይወሳሰብም—ፊልጵ. 1፡19-25፤ 4፡5-9።

   ሐ. ኢዮብ የላቀ በሆነው የኋላ ታሪኩ እየኖረ እና በተመሰቃቀለው አሁኑ ላይ እየቃተተ ነበር (ኢዮብ 29፡1—30፡31)፤ ከቅንነቱ፣ ከጽድቁ፣ ከግብረገባዊነቱ እና ከፍጽምናው ጋር ያለማቋረጥ ተጣብቆ እና ይመካም ጭምር ነበር (27፡1-7፤ 31፡1-40)፦

      1. ጳውሎስ ግን ሙሉ በሆነ መጠን የአሁኑን "የዛሬ ክርስቶስ" ለማግኘት ከኋላው የነበሩትን ነገሮች ለመርሳት ራሱን አስለመደ—ፊልጵ. 3፡8፣ 13-14።
      2. በተጨማሪም፣ ጳውሎስ የትናንት ሰው ሳይሆን የዛሬ ሰው ነበር (ዕብ. 3፡7-8፣ 15፤ መዝ. 95፡7-8)፤ ወደ ፊት አሻግረን መመልከት እና ወደ ኋላ ተመልሰን መመልከት የለብንም፤ የዛሬ ሰዎች ነን (ማቴ. 6፡11፣ 33-34፤ ሉቃ. 19፡9-10፤ 23፡43)።
      3. የምንወደው ክርስቶስ በምድር ላይ ሰማያዊ ሕይወት እንድንኖር ደግፎ የሚያስቀጥለን የየዕለት ድነታችን እና የአፍታ አፍታ አቅርቦታችን የሆነ የአሁን ክርስቶስ፣ የዛሬ ክርስቶስ እና በሰማያት በዙፋን ላይ ያለ ክርስቶስ ነው—ማቴ. 28፡20፤ 1 ጴጥ. 1፡8፤ ዕብ. 8፡2፤ 4፡14-15፤ 7፡26፤ 2 ቆሮ. 6፡2፤ ሮሜ 5፡10።
      4. ሙሉ በሙሉ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስንሆን፣ በዘላለም ውስጥ እያንዳንዱ ቀን ዛሬ ስለሆነ ዛሬ ይኖረናል፤ ያለን ብቸኛው ቀን ዛሬ እንጂ ነገ አይደለም።

   መ. ለሦስቱ ባልንጀሮቹ በነበረው ስምንት የንግግር ጊዜያት በኩል፣ ኢዮብ የሚከተሉት መለያ ባሕርያት እንዳለው ሰው ራሱን አጋለጠ፦

      1. ኢዮብ ራሱን-የሚያጸድቅ ነበር (ኢዮብ 6፡30፤ 9፡20፤ 27፡5-6፤ 32፡1)፤ በፍጥረታዊ ማንነቱ ስኬት እና ግኝቶች ጨልሞ፣ በሆነው ነገር ረክቶ ነበር፣ ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለነበረው የተመሰቃቀለ ሁኔታ አያውቅም ነበር (ተዛ. ፊልጵ. 3፡9፤ ራእ. 3፡17-18)።
      2. ኢዮብ ለእግዚአብሔር እውቅና የሰጠው በስም እንጂ በእውነታ አልነበረም፤ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን በእግዚአብሔር የተጥለቀለቀ፣ በእግዚአብሔር የተሞላ እና ከእግዚአብሔር ጋር የተዋሐደ አልነበረም—መዝ. 92፡10፤ ዘሌ. 2፡4-5፤ ሮሜ 8፡16፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ኤፌ. 3፡19፤ 5፡18፣ 26፤ ዕብ. 2፡10-11።
      3. ኢዮብ እግዚአብሔርን ለዘላለም ለመኖር እና ለመግለጥ የሆነ እንደ የእግዚአብሔር ሕይወታዊ አካል የአዲሲቱ ኢየሩሳሌምን አንዳች ገጽታ እና አንዳች ባሕርይ የሚያመለክት ንጥረ-ነገር አልነበረውም፤ ከዚህ በተነጻጻሪ፣ የእግዚአብሔር ስም፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስም እና የጌታ ስም በድል-ነሺው ላይ ተጽፈዋል፣ ይህም እግዚአብሔር የሆነው፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ባሕርይ እና የጌታ ማንነት በሙሉ ወደ ድል-ነሺው ውስጥ መሠራታቸውን ያመለክታል—ራእ. 3፡12።

   ሠ. አማኞች እየተሰቃዩባቸው ያሉት መከራዎች ለዘላለም ያተርፉት እና ይደሰቱት ዘንድ የክብር አምላክ የከበረ እድል-ፈንታቸው የሚሆንበት የክብርን የዘላለም ብዛት እንደሚሠራላቸው ለአዲስ ኪዳን አማኞች በማወጁ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳደረገው፣ ኢዮብ ወይም ባልንጀሮቹ እግዚአብሔር እርሱን ያደበበትን አላማ አላወቁም—2 ቆሮ. 4፡17።

ረ. ኢዮብ እና ባልንጀሮቹ በትህትና መንፈስ እና በጸሎት መንፈሳቸውን በማንቀሳቀስ እግዚአብሔርን ለመሻት ጊዜ ወስደው ቢሆን ኖሮ (ኢሳ. 57፡15፤ 66፡2፤ ቆላ. 4፡2)፣ ዳግም የተወለደ፣ የተለወጠ እና የከበረ በክርስቶስ የሆነ ቅዱስ ከፍጥረታዊው ሰው ጋር ምንም ጉዳይ እንደሌለው እና በፍጥረታዊ ሰናይ ባሕርያት ራሱን መገንባት እንደማያስፈልገው እግዚአብሔር ሊያሳያቸው ይችል ነበር።

ሰ. በጨለማ ውስጥ የሚዋትቱ የዕውር ሰዎች ቡድን እንደሆነ ዘገባ በሠላሳ-አምስት ምዕራፎች ውስጥ ካሉ ከጊዜ-አባካኞች፣ ከሕመም-ጨማሪዎች እና ከንቱ ከሆኑ ክርክሮች ይህ ሰማያዊ ራእይ ያድናቸው ነበር፤ ስለ እግዚአብሔር አውርተዋል መንፈሳቸውንም ጠቅሰዋል (ኢዮብ 32፡8)፣ ነገር ግን ሁሉም እግዚአብሔርን ይነኩ እና እንደ ሕይወታቸው፣ ብርሃናቸው እና መንፈሳዊ አቅርቦታቸው እግዚአብሔርን ይቀበሉ ዘንድ ለኢዮብ ለመጸለይ እና አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ኅብረት ለማድረግ መንፈሳቸውን በማንቀሳቀስ ፈንታ ሦስት ዙር በሆኑ ረጅም ክርክሮች አእምሮአቸውን አንቀሳቀሱ፦

1. ሕያው-ንቁ ቡድኖች የሚኖሩን ከሆነ፣ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት በእነዚህ ንግግሮች ማስጠንቀቂያ መቀበል አለብን፤ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ የምናየው ቡድን አሉታዊ ምሳሌ ይሰጠናል፤ በዛሬው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሊኖረን የማይገባ የቡድን አይነት ነው፤ አንድ ላይ ስንሰባሰብ ማድረግ ያለብን የመጀመሪያው ነገር ለመጸለይ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ነው፤ ሕያው-ንቁ ቡድኖች የሕያው-ንቁ ጸሎት ቡድኖች ናቸው—ተዛ. ሐዋ. 12፡5፣ 11-12፤ ዕብ. 10፡24-25፤ 3፡13።
2. ቡድኖቹ ሕያው-ንቁ የሆኑት በእነዚህ ሁለት መንፈሶች ነው—በሰው መንፈሳችን ሕያው-ንቁ እና በእግዚአብሔር መለኮታዊ መንፈስ ሕያው-ንቁ፤ የክርስቲያን ሕይወት አንድ መንፈስ ለመሆን እንደ ሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ዳግም በተወለደው መንፈሳችን ውስጥ እና ዳግም ከተወለደው መንፈሳችን ጋር የተዋሐደው የተጠናቀቀው መንፈስ ሕይወት ነው—ዮሐ. 4፡24፤ ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ገላ. 3፡14፤ 6፡18።
3. መለኮታዊውን መንፈስ በመንፈሳችን መንካትን መማር ያስፈልገናል፤ የክርስቲያን ሕይወት እና ሥራ ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ይህ ነው፤ ይህ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ አካሉን ለመገንባት እና ሙሽራውን ለማዘጋጀት ራሱን በክርስቶስ እንደ መንፈስ ወደ ሰው ውስጥ ለማደል የሆነውን ኢኮኖሚውን፣ እቅዱን ለመፈጸም የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ በሰው ውስጥ እና የሰው እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር ውስጥ ነው—2 ቆሮ. 2፡13፤ ፊልጵ. 3፡3፤ ሮሜ 1፡9።
4. ጳውሎስ የሆንነው ነገር ሁሉ (2፡29፤ 8፡5-6፣ 9)፣ ያለን ነገር ሁሉ (ቁ. 10፣ 16) ወደ እግዚአብሔር የምናደርገው ነገር ሁሉ (1፡9፤ 7፡6፤ 8፡4፤ 12፡11) በመንፈሳችን መሆን እንዳለበት በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ አጽንኦት ይሰጣል፤ በመንፈስ የሆኑ ሰዎች ለመሆን ፍጹም መደረግ እና መገንባት አለብን፤ የእግዚአብሔር አፍቃሪ ለመሆን፣ የክርስቶስ ፈላጊ ለመሆን ወይም ድል-ነሺ ለመሆን በመንፈስ ከመሆን ውጪ ሌላ መንገድ የለም (ራእ. 1፡10፤ 4፡2፤ 17፡3፤ 21፡10)።

## II. በብሉይ ኪዳን ያለው የኢዮብ የእግዚአብሔርን መጨረስ እና መግፈፍ ልምምድ በአዲስ ኪዳን ካለው ከጳውሎስ የራቀ ነበር—1 ጢሞ. 1፡16፦

ሀ. የእግዚአብሔር መጨረስ እኛን ባዶ ለማድረግ (ለማሳለቅ) ሲሆን፣ የእግዚአብሔር መግፈፍ ክርስቶስን ለመግለጥ ክርስቶስን መኖራችንን የሚተካውን የፍጥረታዊ ግብረገባዊነታችንን—በባሕሪያችን ውስጥ ያለውን የፍጥረታዊ ፍጽምናችንን እና ቅንነታችንን—ለማፈራረስ እና ለመውሰድ ነው—ፊልጵ. 1፡19-20፤ 3፡4-9።

ለ. ቀን በቀን እና ሰዓት በሰዓት፣ ኢዮብ ሳይደሰት እየተጨረሰ ነበር፣ በአዲስ ኪዳን ግን፣ የእግዚአብሔር መጨረስ እና መግፈፍ የሚያስደስቱ ነገሮች ሆነዋል፤ ከተለወጠበት ጊዜ አንሥቶ፣ ጳውሎስ በጌታ እንዳለ እስረኛ በእግዚአብሔር መጨረስ እና መግፈፍ ሥር የነበረ ሰው ነበር፣ ሆኖም ግን በደስታ እና በሐሴት የተሞላ ነበር—ሐዋ. 9፡15-16፤ 2 ቆሮ. 4፡16፤ ፊልጵ. 1፡19-21፤ ኤፌ. 3፡1፤ 4፡1፤ ፊልጵ. 1፡4፣ 18፣ 25፤ 2፡2፣ 17-18፤ 28-29፤ 3፡1፤ 4፡1፣ 4።

ሐ. ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ ነበር፤ በመቆም (በማክተም) እና በሙብቀል በኩል እንደገና መወለድ የተሰቀሉ ሆኖ ዳግም መወለድ ነው (ዮሐ. 3፡5፤ ሮሜ 6፡4፤ ቆላ. 2፡12)፤ እኛ፣ እንደ ጳውሎስ፣ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ የምንኖረው እኛ ሳንሆን ክርስቶስ በእኛ ለመኖሩ (ገላ. 2፡20) ለሆነ አላማ የተሰቀልን ሆነን እንደገና ተወልደናል።

መ. አሁን በክርስትና ሕይወታችን ለመኖር እየሞትን ነው (ቁ. 20፤ 1 ቆሮ. 15፡31፣ 36፤ ዮሐ. 12፡24፤ 2 ቆሮ. 4፡11)፤ ለመኖር መሞት መስቀሉን የመሸከም ትክክለኛ ትርጉም ነው (ማቴ. 16፡24-26፤ ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ #622)።

ሠ. የእግዚአብሔርን መጨረስ እና መግፈፍ በመለማመዱ ውስጥ፣ ጳውሎስ ከሁሉም አቅጣጫ በሚመጡት ግፊቶች ሥር አልተገደበም የተጣለ ቢሆንም አልጠፋም፤ ጳውሎስ የተወለደበትን ቀን አልረገመም፣ ከመኖር ይልቅ መሞት እንደሚመርጥ አልተናገረም፤ በተቃራኒው፣ ከብዙ ማጤን በኋላ ጳውሎስ ስለ ቅዱሳን መገስገስ (በሕይወት ስለማደጋቸው) እምነትን ስለ መደሰታቸው (ስለ ክርስቶስ ድሰታቸው) አሁንም ለመኖር እንደሚመርጥ ተናግሯል—2 ቆሮ. 1፡8-9፤ ገላ. 2፡20፤ ፊልጵ. 1፡21-25።

ረ. ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ሲል በጭንቀቶች ሲሰቃይ (2 ቆሮ. 12፡10)፣ ስለ ልምምዶቹ በጌታ በጣም ተደስቶ ነበር፣ ደስተኛ ነበር፣ እንዲያውም ሀሴት እያደረገ ነበር (ቆላ. 1፡24፤ ፊልጵ. 2፡17-18)።

ሰ. ጳውሎስ የክርስቶስን ሞት ለመምሰል ክርስቶስን፣ የትንሣኤውን ኃይል እና በመከራው መካፈልን ለማወቅ ፈለገ (3፡10)፤ የክርስቶስን ሞት ለሕይወቱ እንደሆነ ቅርጽ ወሰደ፣ እንዲሁም በክርስቶስ ሞት ቅርጽ ውስጥ መግባት ታላቅ ደስታው ነበር።

ሸ. ጳውሎስ በሕይወት ይሁን በሞት በተትረፈረፈው የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ አቅርቦት ክርስቶስን በመኖር አጎላው፤ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር፣ ሰው እንዲኖር ይፈልግ የነበረው የሕይወት አይነት ይህ ነበር—1፡19-21፤ ዘፍ. 1፡26።

ቀ. ጳውሎስ የኢየሱስ ሕይወት በሚሞት ሥጋው ይገለጥ ዘንድ ስለ ኢየሱስ ሲል ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት፣ መገደል፣ በሥጋው ተሸክሞ ይዞር እና ለሞት አልፎ ይሰጥ እንደነበር ተናግሯል፤ በጌታ ሞት መገደል ሥር ስንሆን፣ የትንሣኤ ሕይወቱ በእኛ በኩል ወደ ሌሎች ይካፈላል—2 ቆሮ. 4፡10-12፡-

1. በከባቢ ሁኔታችን ያለው የኢየሱስ መሞት ሥጋችንን እና ነፍሳችንን ያቀፈውን ፍጥረታዊ ሰዋችንን (ውጫዊው ሰዋችንን) ለመግደል በውስጥ ከሚያድረው መንፈስ ጋር ይተባበራል፤ በሞት የመግደል ሥራ የውጫዊው ሰዋችን ሲጠፋ ሳለ፣ በትንሣኤው ሕይወት ትኩስ አቅርቦት የውስጡ ሰዋችን ዕለት ዕለት እየታደሰ ነው—ቁ. 16።
2. ጳውሎስ ዕለት ዕለት እንደሚሞት ተናግሯል (1 ቆሮ. 15፡31)፤ በየዕለቱ ለሞት ራሱን አጋለጠ፣ ሞትን ተጋፈጠ፣ ለእኔነትም ሞተ (2 ቆሮ. 11፡23፤ 4፡11፤ 1፡8-9፤ ሮሜ 8፡36)።
3. የክርስቶስ ሞት እና ፍቱንነቱ መተግበር ያለው የክርስቶስን ሞት እና ፍቱንነቱን ከመንፈሳችን ወደ ነፍሳችን እና ወደሚሞተው ሰውነታችን እንኳን ሳይቀር ለማደል በመንፈሳችን ውስጥ በሚያድረው በተቀመመው መንፈስ ውስጥ ነው—ዘጸ. 30፡22-25፤ ሮሜ 8፡6፣ 9-11።
4. ይህ እደላ መቀባቱ ነው (1 ዮሐ. 2፡20፣ 27)፣ መቀባቱ ደግሞ በውስጥ የሚያድረው መንፈስ መንቀሳቀስ ነው፤ ጸሎታችን በውስጥ የሚያድረውን መንፈስ ያንቀሳቅሰዋል፣ በዚህ እንቅስቃሴም ውስጥ የመግደል ኃይል አለ።

በ. የእግዚአብሔርን መጨረስ እና መግፈፍ በመለማመዱ ውስጥ፣ ጳውሎስ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናል ብሏል፤ ዘላለም ከየጊዜው ጋር በንጽጽር ተቀምጧል፣ ብዛት ከቀላል ጋር በንጽጽር ተቀምጧል፣ እንዲሁም ክብር ከመከራ ጋር በንጽጽር ተቀምጧል—2 ቆሮ. 4፡16-17፤ ሮሜ 8፡28-29።

ተ. ኢዮብ በመከራ መሰቃየቱን በጣም ከባድ እንደሆነ ነገር አድርጎ ቆጥሮታል፣ ጳውሎስ ግን መከራውን ጊዜያዊ እና ቀላል አድርጎ ቆጥሮታል፤ ስለ መከራችን ግድ በመሰኘት ፈንታ፣ ከአንድ የክብር መጠን ወደ ሌላ በመለወጣችን እንደ የክብር ብዛት ለእግዚአብሔር በውስጣችን መጨመር ግድ መሰኘት ያስፈልገናል፤ ብዙ እግዚአብሔር በውስጣችን እስካለን ድረስ፣ የእውነት የሚያስፈልገው ይህ ነው—ሐዋ. 7፡2፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ቆላ. 2፡19፡-

1. እንደ ጳውሎስ፣ ፍጥረታዊ ሰዋችንን ለመግደል ከመንፈስ ጋር በሚሠራው በመከራ እና በመጨመቅ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ ነን፤ በውስጥ ከሚያድረው መንፈስ ጋር መተባበር እና በመንፈሳችን፣ በነፍሳችን እና በሥጋችን ያለውን ውጫዊ ከባቢ ሁኔታ መቀበል አለብን፣ ምክንያቱም የምንመለከተው የሚታዩትን የጊዜያዊ መከራ ነገሮችን ሳይሆን የማያታዩትን የዘላለም ክብር ነገሮች ነውና—ፊልጵ. 1፡19-20፤ 2 ቆሮ. 4፡18፤ ዕብ. 11፡1፣ 27፤ 2 ቆሮ. 5፡7።
2. በሚገድለው ከባቢ ሁኔታችን መካከል ለመደሰት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ያስፈልገናል (ፊልጵ. 4፡4)፤ እኛን እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲስ ለማድረግ የውስጡ ሰውነታችን በመታደሱ ሕይወቱ በሰውነታችን ይገለጥ ዘንድ የጌታ ሉአላዊነት በክርስቶስ ሞት መግደል ሥር እኛን ለማስቀመጥ እየሠራ ነው (2 ቆሮ. 4፡10-12፣ 16፤ 5፡17፤ ገላ. 6፡15፤ ራእ. 21፡2፣ 5፣ 10)።

© 2020 Living Stream Ministry